Australian Government

COVID-19 VACCINATION

# ኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች: የተለመዱ ጥያቄዎች

ይህ መረጃ በቀን 13 ጥቅምት/October 2021 ዓ.ም ትክክለኛ እንደሆነ ነው።

## ኮቪድ/COVID-19 ክትባት ለምድ ነው መውሰድ ያለብኝ?

ኮቪድ/COVID-19 በጣም ከባድ ህመም ሊሆን ይችላል። በተይ ደግትሞ በማህበረሰባችን ውስጥ በቀላሉ ሊጠቁ ለሚችሉት አደገኛ ይሆናል። ለእርስዎና ለማህበረሰብዎት በጣም ህመም ወይም በኮቪድ/COVID-19 መሞትን ለመከላከል ክትባቱን መውሰድ በጣም ጥሩ የሆነ ዘዴ ነው።

ቀደም ሲል በተገኘ ማስረጃ እንደሚያሳየው የኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች ቫይረስ ስርጭትን ለመቀነስ እንደሚረዳ ነው። እኛ ክትባት በመውሰድ ለቫይረስ ስርጭት መቀነስ እንችላለን።

ኮቪድ/COVID-19 የሰውን ኑሮ ህይወት ቀይሮታል። አብዛኛው ሰው ክትባቱን ከወሰዱ የኮቪድ/COVID-19 ወረርሽኝ መፈጠር እድል በጣም ያነሰ እንደሚሆን ነው።

## ኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች እንዴት ይሰራሉ?

ኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች እንደሌሎች ክትባቶች ይሰራል። ክትባቶች የሚረዱት የአንድ ሰው ሰውነት ህመም ሊፈጥር የሚችልን ቫይረሶች ለይቶ ስለሚዋጋ ነው። የኮቪድ/COVID-19 ክትባት የሚረዳው ሰውነት ለኮቪድ/ COVID-19 ምክንያት ለሚሆን ቫይረስ ለይቶ ለማወቅና ለመዋጋት ነው።

## የኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች ደህንነታቸው የተጠበቀ ነው ወይ?

የህክምና ጥራት አስተዳደር (TGA) በሳይንቲሶችና በህክምና ባለሙያ ኤክስፐርቶች በአውስትራሊያ ውስጥ ለሚጠቀሙት ክትባቶችና መድሃኒቶች እንዲሁም ለሌላ ህክምና ምርቶች በመቆጣጠር ተቀባይነት እንዳለው ያጸድቃሉ። በአውስትራሊያ ውስጥ ለኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች በሙሉ ለመጠቀም ተቀባይነት ከማግኘታቸው በፊት ስላላቸው ጥራት፤ ደህንነት እና በጥሩ መስራቱን የ TGA ያጣራል። በአውስይራሊያ ውስጥ ለክትባቶች በሙሉ የሚካሄደው አሰራር ተመሳሳይ ነው።

በ TGA ውስጥ ያሉት የህክምና ኤክስፐርቶች ሁሉም ክትባቶች ደህንነታቸው የተጠበቀ ስለመሆኑ በተከታታይ ያጣራሉ። በአውስትራሊያ ውስጥ ክትባቶች መጠቀም የሚፈቀደው ጥናት ከተካሄደና ተቀባይነት ካገኘ በኋላ እንደሆነ እና ከሚያስከትለው ችግር የሚያስገኘው ጥቅም የበለጠ ሆኖ ስለተገኘ ነው።

## የኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች እንዴት በፍጥነት ተፈጠሩ?

ኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች ሲወጡ ደህንነቱ የተጠበቀና በጥሩ እንደሚሰሩ ነበር። ይሁን እንጂ በዓለም ዙሪያ ያሉት ተመራማሪዎች ወረርሽኙ ከጀመረ አንስቶ ለኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች ለመፍጠር በከባድ ጥረት በጋር ይሰሩ እንደነበር ነው። ሌሎች ክትባቶችም ተመሳሳይ የአሰራር ሂደት እርምጃዎች ይወስዱ እንደነበር ነው።

ደህንነቱ የተጠበቀና ጥሩ የሚሰሩ ኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች በፍጥነት የተፈጠሩበት ምክንያት:

- በምርመራ ጥናት እና ለማምረት ከፍተኛ መጠን የገንዘብ እርዳታ ስለወጣ
- የአዲስ ተክኖሎጂዎች አቅርቦት መኖር የእድገት መሻሻል ለማቀላጠፍ
- በሞላው ዓለም ዙሪያ ያሉት ተመራማሪዎች፣ ሳይንቲስቶች እና አምራቾች በጋር ስለሚሰሩ ነው
- አንዳንድ የክሊኒካል ሙከራዎች ደረጃዎች እና በተመሳሳይ ጊዜ የሚካሄደው የተቀባይነት አሰራር ሂደት በተናጠል ሳይሆን በጋራ በተመሳሳይ ጊዜ ስለሆነ ነው።

ይህ እኛ ክትባቱን በተቻለ ፍጥነት እንድናቀርብ አድርጓል።

## እንዴት የኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች ይከላከሉልናል?

ኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች ለርስዎ ሰውነት ኮቪድን/COVID-19 ለይቶ እንዲዋጋ ያስተምራል። ለኮቪድ/COVID-19 እንደማይዙ ናቸው። ክትባቱን በመውሰድ ኮቪድ/ COVID-19 አይዝዎትም። ክትባቶቹ ደህንነታቸው በተጠበቀ መንገድ ለመከላከል ህመም ሳይፈጥር በሰውነት ውስጥ ካለው ቫይረስ ጋር ይዋጋሉ።

በአውስትራሊያ ውስጥ ለመጠቀም ተቀባይነት ባገኙት የኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች እንዳሳዩት ከፍተኛ ህመም፣ ወደ ሆስፒታ መሄድና ሞት ከሚፈጥሩት ጋር በመዋጋት በጣም ጥሩ የሆነ መከላከያ እንደሆኑ ናቸው።

ስለ ኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች ከሀኪምዎ ጋር መነጋገር እንደሚችሉ እና ለዚህ ነው የማህበረሰቡን ደህንነትና ጤና ለመጠበቅ ክትባት መውሰዱ ጠቃሚ አካል የሆነው።

## ከኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች ምን ዓይነት ችግር እንደሚፈጠር መገመት አለብኝ?

ክትባቶች በሙሉ አንዳንድ ችግር ሊፈጥሩ ይችላሉ። እነዚህ የሚከሰቱት ችግሮች በአብዛኛው መካከለኛና ለጥቂት ቀናት ብቻ ነው የሚቆዩት።

በሚፈጠር ችግሮች ላይ መካተት የሚችሉት:

- መርፌውን ከወሰዱ በኋላ በክንድ ላይ ህመም
- ትኩሳት
- የጅማት ህመም
- የራስ ምታት ናቸው።

ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ ጥያቄዎች ወይም አሳሳቢ ጉዳይ ካለዎት ለርስዎ ክትባት የሰጠን ክሊኒክ ወይም ሀኪም ማነጋገር።

በአስትራዘነካ/AstraZeneca ክትባትና በጣም መጠነኛ የሆነ ደም መርጋትና በአነስተኛ የሆነ የደም ፕላተለት/platelet መጠን ደረጃ ስለመፈጠር ግንኙነት እንዳለ ነው። ስለዚህ በበለጠ ለማንበብ ድረገጽ:
https://www.health.gov.au/resources/publication/astrazeneca-information-other-languages

## የኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች ለቫይረሱ መሰራጨት ይቀንሳልን?

ከመታመምዎት በፊት፣ ወደ ሆስፒታል ምሄድዎ፣ ወይም በኮቪድ/COVID-19 መሞትዎ በፊት ለመከላከል የኮቪድ/COVID-19 ክትባት በጣም እንደሚሰራ ነው። እንዲሁም ቀደም ሲል ባለ ማስረጃ እንደሚያሳየው ኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች ለቫይረስ ስርጭት እንዲቀንስ እንደሚረዱ ናቸው።

በምርመራ ጥናት ማስረጃ እንደሚለው የሆነ ሰው ክትባቱን ከወሰደ በኋላ በኮቪድ/COVID-19 ከታመመ እና ክትባቱን ካልወሰዱ ሰዎች ጋር ሲነጻጸር በሌላ ሰው ላይ ለሚከሰት ህመም በጣም የቀነሰ ነው።

## የኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች በነብሰጡር ወይም ጡት በሚያጠቡ ላይ ችግር ያመጣል ወይ?

እርጉዝ፣ ጡት የሚያጠቡ ወይም ለማርገዝ እቅድ ካለዎት የኮሚርናትይ/Comirnaty (ፕፊዘር/Pfizer) ወይም የስፒከቫክስ/Spikevax (ሞደርና/Moderna) COVID-19 ክትባትን ቢወስዱ ይመረጣል። በሞላው ዓለም የምርመር ጥናት እንደሚያሳየው የፕፊዘር/Pfizer እና የሞደርና/Moderna ክትባቶች ለእርጉዝና ጡት ለሚያጠቡ ሴቶች ደህንነቱ የተጠበቀ እንደሆነ ነው።

ኮቪድ/COVID-19 ከያዝዎት፤ እርስዎና ያልተወለደው ህጻንዎ አደጋ ላይ ሊሆኑ ይችላል። በዚህ የሚኖር:

- ወደ ሆስፒታል ለመሄድ ከፍተኛ ችግር
- ህጻኑ ያለጊዜው ቀድሞ የመወለድ እድል መኖርና ወደ ሆስፒታል መሄድ አስፈልጊነት
- ህጻኑ በሞት የመወለድ መጠነኛ ከፍተኛ ችግር (ህጻን ያለ ህይወት መወለድ)።

ችግር ለመቀነስ በጣም ጥሩ የሆነው ዘዴ በማንኛውም የእርግዝና ግዜ ኮቪድ/COVID-19 ክትባትን ማግኘት ይሆናል።

ጡት የሚያጠቡ ከሆነና ለፐፊዘር/Pfizer ወይም ለሞደርና/Moderna ክትባት ማግኘት ካልተቻለ፤ ክትባት በመውሰድ ከሚፈጠረው ችግር የሚመጣው ጥቅም የበለጠ ከሆነ ለአስትራዘኒካ/ AstraZeneca ክትባት ለመውሰድ ግምት ውስጥ ማገባት።የትኛውንም ክትባት ቢወስዱም ነገር ግን ቅድሚያ የልጅዎን ጡት ማጥባት ማቆም የለብዎትም።

እርጉዝ ወይም ጡት የሚያጠቡ ከሆነ ስለ ኮቪድ/ COVID-19 ክትባቶች ድህንነት መረጃ ለማግኘት ሀኪምዎን ማነጋገር ይችላሉ። ማግኘት ይችላሉ። የበለጠ መረጃ ማግኘት የሚቻለው ድረገጽ: www.health.gov.au/resources/translated/pregnancy-and-covid-19-vaccines-other-languages

## ኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች ላለመውለድ ችግር ይፈጥራልን?

የኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች በሴቶችም ሆነ በወንዶች ላይ ላለመውለድ ችግር መፍጠር እንዳለ የሚያሳይ ሳይንሳዊ መረጃ የለም።

አውስትራሊያ ውስጥ ድህንነቱና ጥሩ ውጤት ያለው ክትባት ካልሆነ በስተቀር የህክምና ጥራት አስተዳደር/TGA ተቀባይነት አይሰጥም። ይህ ማለት ክትባቱ በወንድ ወይም ሴት ላይ ያለመውለድ ችግር ካለበት ክትባቱ በ TGA ተቀባይነት አያገኝም። በማንኛውም TGA ባጸደቀው ኮቪድ/COVID-19 ክትባት ላይ በተደረገ ጥናት ላለመውለድ የተገኘ ችግር እንደሌለ ነው።

## ኮቪድ/COVID-19 ክትባቶችን ማን ነው ማግኘት የሚችል?

በአውስትራሊያ ውስጥ እድሜው 12 ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆነ እያንዳንዱ ሰው በነጻ ክትባቶችን ማግኘት ይችላል። በመንግሥት ክትባት መስጫ ክሊኒክ በኩል የርስዎን ክትባት የሚወስዱ ከሆነ የመዲኬር ካርድ አያስፈልግዎትም። ለኮቪድ/COVID-19 ክትባት መስጫ ክሊኒክ ለማግኘትና ቀጠሮ ለማቀናጀት የሚችሉት፤ በክትባት ክሊኒክ መፈለጊያ/vaccine clinic finder ድረገጽ መጠቀም: finder https://covid-vaccine.healthdirect.gov.au/

## ህጻናት ኮቪድ/COVID-19 ክትባት መውሰድ ይችላሉን?

እድሚያቸው 12 ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆኑት ህጻናት ለPfizer ወይም Moderna ኮቪድ/COVID-19 ክትባት ማግኘት ይችላሉ።

የአውስትራሊያ በሽታ መከላከያ ክትባት ኤክስፐርቶች፤ የአውስትራሊያ በሽታ መከላከያ ክትባት ተክኒካል አማካሪ ቡድን (ATAGI), በተሰጠው ምክር መሰረት እድሚያቸው 12 ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆኑት ህጻናት የፊዘር/Pfizer ወይም ሞደርና/Moderna ክትባቶችን መጠቀም እንደሚችሉ ነው።

ለራስዎና ቤተሰብዎ የትኛው ክትባት ትክክለኛ ስለመሆኑ ለማወቅ ሀኪምዎን ማነጋገር ነው።

## ሁለት መጠን/ doses የኮቪድ/COVID-19 ክትባት ያስፈልገኛል ወይ? ለኮቪድ/COVID-19 ክትባት ሥራ ውጤት ሁለቱም አንድ ዓይነት መሆን አለባቸውን?

አዎ፡ በ ATAGI ህክምና ኤክስፐርቶች እንዳሉት አንድ ዓይነት ክትባት በሁለት ጊዜ መጠን/dose መውሰዱ እንደሚያስፈልግ ነው። እንዲሁም ይህ በ TGA ስለሚሰጠው ቀጣይነት ላለው ይሆናል።

ክትባቱን የሚያቀርብልዎት ሰው ምን ዓይነት ክትባት ማግኘት እንዳለብዎት ያሳውቅዎታል እንዲሁም የሚኖርዎት ሁለተኛው ቀጠሮ መቸ እንደሆነ ይነግርዎታል።

## ሶስተኛ መጠን/dose የኮቪድ/COVID-19 ክትባት ያስፈልገኛልን?

በአውስትራሊያ በሽታ መከላከያ ክትባት ኤክስፐርቶች፤ ATAGI የተሰጠው ምክር እድሚያቸው ከ12 ዓመት በላይና ከባድ የበሽታ መቋቋም ሀይል ለተዳከመ (severely immunocompromised) ሰዎች ሶስተኛ መጠን/dose የኮቪድ/COVID-19 ክትባት መውሰዱ ይመረጣል። በከባድ የበሽታ መቋቋም ሀይል ያሉት ሰዎች ከሌላው ህዝብ ጋር ሲነጻጸር አነስተኛ የበሽታ መቋቋም አቅም እንዳላቸው ነው። ከሌሎች በሁለት መጠን/dose እንደሚያገኙት መከላከያ ተመሳሳይ ለማግኘት እነዚህ ሶስተኛ መጠን/dose ማግኘት አለባቸው።

እነዚህ ለሶስተኛው የሚፈቀድላቸው የሁለተኛ መጠን/dose ክትባት ከወሰዱ በኋላ ከሁለት እስከ ስድስት ወራት ባለው ጊዜ ሶስተኛ መጠን/dose የኮቪድ/COVID-19 ክትባት መውሰድ አለባቸው።

በከባድ የበሽታ መቋቋም ሀይል መዳከም ላይ ላልሆኑ ሰዎች በዚህ ደረጃ ላይ ለሶስተኛ መጠን/dose የኮቪድ/COVID-19 ክትባት መውሰድ የለባቸውም፤ ምክንያቱም በወሰዱት የሁለት መጠን//dose ክትባት ለቫይረሱ ለመከላከል በቂ መቋቋሚያ ስላላቸው ነው።

## ለእኔ ኮቪድ/COVID-19 ክትባት እንዴት ቀጠሮ ማስያዝ እችላለሁ?

ክትባት መስጫ ክሊኒክ ማግኘትና ለኮቪድ/COVID-19 ክትባት ቀጠሮ ማግኘት የሚችሉት ለክትባት ክሊኒክ መፈለጊያ/vaccine clinic finder በመጠቀም ሲሆን ድረገጽ፡ https://covid-vaccine.healthdirect.gov.au/

እንዲሁም ለርስዎ ክትባት ቀጠሮ ስለማስያዝ ለርስዎ ሀኪም ወይም ለማህበረሰብ ተሳታፊ ፋርማሲስት ማነጋገር ይችላሉ።

## አውስትራሊያ ውስጥ ኮቪድ/COVID-19 ክትባቶችን መውሰድ ግዴታ ነውን?

ለኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች መውሰድ በፈቃደኝነት ነው። ሰዎች ስለ ኮቪድ/ COVID-19 ክትባት መውሰድ ፍላጎት በራሳቸው ምርጫ ይሆናል። ለኮቪድ/ COVID-19 ክትባት ስላልወሰዱ የገንዘብ ቅጣት አያገኙም።

በእድሜ አንጋፋ እንክብካቤ መስጫ መኖሪያ ለሚሰሩ ሰዎች የጸረ-ኮቪድ/ COVID-19 ክትባትን መውሰድ ይኖርባቸዋል። አንዳንድ አስተዳደር ግዛቶችና ተሪቶርስ ለክትባት አሰጣጥ አስፈላጊነት በራሳቸው ያወጡት ሊኖር ይችላል። በጤና ሁኔታዎች ምክንያት ክትባት መውሰድ ለማይችሉ ሰዎች ነጻ ለሚያደርጓቸው ይቀመጣል።

## ከክትባቶቹ አንዱን በውጭ አገር መውሰድ እችላለሁን?

አውስትራሊያ ውስጥ ያሉት ሰዎች የኮቪድ/ COVID-19 ክትባት መውሰድ የሚችሉት በTGA ተቀባይነት ላላቸው ክትባቶች ብቻ ነው። እንዲሁም እነዚህ ክትባቶች በሌሎች አገሮች ለመጠቀም ተቀባይነት ያገኙ ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ክትባቶች ደህንነታቸው ያልተጠበቀ ወይ የውሸት ሊሆኑ ስለሚችሉ፤ በኦንላይን መስመር ኮቪድ/ COVID-19 ክትባት መሞከርና መግዛት የለብዎትም።

## ክትባቱን ከወሰድኩ በኋላ ለኮቪድ/COVID-19 ስርጭት ለማቆም አሁንም ሌላ ጥንቃቄዎችን መውሰድ አለብኝ ወይ?

ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ ለኮቪድ/COVID-19 ስርጭት ለማቆም አሁንም ጠቃሚ የሆኑ የደህንነት እንቅስቃሴዎችን መቀጠሉ ለርስዎ ጠቃሚ ነው።

ከሌሎች ሰዎች እርቀትዎን በ 1.5 ሜትር ሆኖ መቀየት፤ በተደጋጋሚ እጆችዎን በሳሙናና ውሃ አድርጎ መታጠብ፤ ከታመሙ እቤትዎ መቆየት፤ ለኮቪድ/COVID-19 ምርመራ ማካሄድና አስፈላጊ ከሆነ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ጭንብል ማድረግ።

## የኮቪድ/COVID-19 ላለባቸው ሰዎች አሁንም ክትባት መውሰድ ያስፈልጋል ወይ?

ኮቪድ/COVID-19 ለነበረባቸና ለዳኑ ሰዎች አሁንም ክትባት መውሰድ አለባቸው። ምክንያቱም ለኮቪድ/COVID-19 የፈጠረው አዲስ ቫይረስ እንደሆነ እና ብክለቱ ከተፈጠረ በኋል የተፈጥሮ በሽታ መቋቋሚያ ሀይል ለምን ያህል ጊዜ መቆየት እንደሚችል ኤክስፐርቶች ስለማያውቁት ነው። ከጊዜ በኋል ለእንደገና በሽታ መከላከያ መቀነስ በጣም የማይመስል ነው። ስለዚህ ክትባቱን መውሰዱ የበሽታ መቋቋም ሀይልን ከፍ በማድረግና የመከላከያ ሀይል ለረጅም ጊዜ እንዲቆይ ያረጋግጣል።

## የኢንፍሎዌንዛ ፍሉ ክትባት ኮቪድ/COVID-19 እንዳይዘኝ ይከላከላል ወይ?

ኢንፍሎዌንዛ (flu) እና ኮቪድ/COVID-19 ሁለቱም ቫይረሶች ናቸው ነገር ግን አንድ ዓይነት ቫይረስ አይደሉም። ኢንፍሎዌንዛ (flu) ክትባት ለበሽታ መቋቋሚያ ሀይል አይሰጥም ወይም ከኮቪድ/COVID-19 አይከላከልም።

የኮቪድ/COVID-19 ክትባት ከኢንፍሎዌንዛ አይከላከልም።የኢንፍሎዌንዛ (flu) እና ኮቪድ/ COVID-19 ክትባቶች ሁለቱም ቫይረሶች እንደሆኑ ነገር ግን አንድ ዓይነት ቫይረስ አይደሉም። ለሁለቱም ኢንፍሎዌንዛ (flu) እና ኮቪድ/ COVID-19 ክትባቶች መውሰዱ ይመከራል፤ ነገር ግን በኢንፍሎዌንዛ (flu) እና ኮቪድ/ COVID-19 ክትባቶች መካከል ለ 7 ቀናት ልዩነት ስለመቆየት ማስታወስ አለብዎት።

## ለአስትራዘነካ/AstraZeneca ክትባት ከመውሰዴ በፊት የደም ማቅጠኛ መድሃኒት መውሰድ አለብኝ ወይ?

የለብዎም፤ ለርስዎ ክትባት ከመውሰድዎ በፊት የደም ማቅጠኛ መድሃኒት አስፈላጊ አይደለም።

በመደበኛ የሚወስዱትን መድሃኒት በሀኪምዎት ካልተነገርዎት በስተቀር በቀጣይነት መውሰድ አለብዎት።

## ኮቪድ/COVID-19 ከተቀየረ የኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች ይሰራሉን?

ሁሉም ቫይረሶች ከጊዜ በኋላ ይቀየራሉ። ይህ ባህሪያዊ ለውጥ/mutation ይባላል። በተከታታይ የሳይንቲፊክ መረጃዎች እንደሚያሳዩት የኮቪድ/ COVID-19 ባህሪያዊ ለውጦችን (mutations) በመዋጋት ጥሩ ውጤት ይኖራቸዋል። እንደ መደበኛ የተቀባይነት አሰራራቸው እና የቁጥጥር አሰራር ሂደት የህክምና ጥራት አስተዳደር (TGA) በቅርበት ሆኖ በማየት መከታተሉን ይቀጥላል።

ይህ ማለት ሰዎች የማነቃቂያ ክትባት እንደ ተታኑስና የመንጋጋ ቆልፍ እና የደረቅ ትክትክ ሳል ያሉት ሊስፈልጋቸው ይችላል፤ ይህ ማለት እንደገና ክትባቱን መውሰድ ሊያስፈልገን ይችላል። ይህ እንደ በየዓመቱ ከኢንፍሉዌንዛ ክትባት ጋር እንደምንወስደው ዓይነት ይሆናል። ተመራማሪዎች አሁንም ይህንን በጥናት እያጣሩት ነው።

ተጨማሪ ማበረታቻ መጠን ስለማስፈለጉ ማለት እንደ ለኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች በየዓመቱ የሚወሰድ ማበረታቻ ክትባት የሚወሰነው አሁንም በተከታታይ በሚካሄድ ክሊኒካዊ ሙከራዎች ተመርኩዞ ይሆናል። ለወደፊት ኮቪድ/COVID-19 ማበረታቻ መውሰድ ስለማስፈለጉና በየስንት ጊዜ የሚለውን ለወደፊት በርስዎ ሀኪም መግለጫ ይሰጥበታል።

## ኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች ያለኝን ዝርያ/genes ወይም DNA ይቀይረዋልን?

አይቀይርም፤ ኮቪድ/ COVID-19 ክትባቶች ያለዎትን ዝርያ ወይም DNA አይቀይርም።

አንዳንድ አዳዲስ ኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች ለRNA (mRNA) መልእክት ማስተላለፊያ እንዲከፋፈል ይጠቅማል፤ ይህም በአንጻር ኮቪድ/COVID-19 ሰውነትዎ የመቋቋም ሀይል እንዲፈጥር መመሪያ ለመስጠት ይሆናል። ይህ ክትባት ለኮቪድ/COVID-19 አይፈጥርብዎትም።

DNA በ mRNA ክትባቶች ውስጥ የተለያየ ዓይነት የ RNA ሞለኩል እንደሆነ ነው። የ mRNA ክትባት በርስዎ DNA ላይ ምንም ዓይነት ነገር እንደማያደርግ እና በሰውነትዎ ውስጥ ከገባ በኋላ ወዲያውኑ ይሰባበራል።

## በክትባቱ የእኔን ዝርያ/genes ወይም DNA ይወስዳልን?

አይወስድም፤ ክትባት በሚወስዱበት ጊዜ፤ ወደ ሰውነትዎ ውስጥ ይገባል። አውስትራሊያ ውስጥ የኮቢድ/ COVID-19 ክትባቶች የሚሰጡት በአብዛኛው በጅማት ውስጥ በላይኛው ክንድ ላይ ይሆናል። የኮቪድ/COVID-19 ክትባት ስለተወጉ የበራሂ ጂናዊ/Genes እና DNA ይወሰዳል ማለት አይደለም።

## ኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች ከኢንተርኔት ጋር ያገናኛል ወይ?

አያገናኝም፤ ኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች አያገናኙኝም – እንዲሁም – ከኢንተርኔት ጋር አያገናኝዎትም። ክትባት የህክምና መድሃኒት ውጤት እንጂ የዲጂታል አይደለም።

## ኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች ለማይክሮቺፕስ ወይም የተክኖሎጂ መቀባበያ አለውን?

ምንም ዓይነት የኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች ሶፍትዌር ወይም ማይክሮቺፕስ አያካትቱም። ለሰዎች መቀባበያ መሆን አይችልም።

## ኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች በመውሰድ ለኮቪድ/COVID-19 ሊያጋልጠኝ ይችላል ወይ?

በአውስትራሊያ ውስጥ ተቀባይነት ያላገኙ የኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች ህይወት ያለው ቫይረስ የያዙት ለኮቪድ/COVID-19 ምክንያት ይሆናሉ። ይህ ማለት የኮቪድ/COVID-19 ክትባት በኮቪድ/COVID-19 እንዲታመሙ እንደማያደርግና ቫይረሱን ከያዙ በኋላ ወደ ሌላ እንዲተላለፍ አያደርግም።

ከኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች አንዳንድ የሚከሰቱ ችግሮች እንደ ትኩሳት፤ የጅማት ህመምና የድካም መንፈስ ሲሆኑ እንደ የኮቪድ/COVID-19 በሽታ ምልክቶች ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ የበሽታ ምልክቶች ክትባቱን ሲወስዱ የሚከሰቱት መደበኛ አካል ናቸው። እነዚህ ክትባቱ ስለመስራቱ የሚያሳዩ ምልክቶች እንደሆኑና ሰውነትዎ ከኮቪድ/COVID-19 ቫይረስ ለመከላከል ሀይል አዳብሯል ማለት ነው።

## የኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች ለእንስሳ ተዋጽኦ ይይዛል ወይ?

በአውስትራሊያ ውስጥ ተቀባይነት ያለው የኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች ምንም ዓይነት የእንስሳ፤ ስጋ ወይም እንቁላል ውጽኢት እንደማይዝ ነው።

## የሃይማኖት መሪዎች ለኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች ምን ዓይነት አስተያየት አላቸው?

በአውስትራሊያ ውስጥ ተቀባይነት ላለው የኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች በብዙ ሃይማኖት መሪዎች ይፈቀዳል።

በቀን 22 ታህሳስ/December 2020 ዓ.ም ለኮቪድ/ COVID-19 ክትባቶች ለመደገፍ የቫቲካን ሃይማኖት ጽሁፋዊ መግለጫ አውጥቷል። የቫቲካን ጽሁፋዊ መግለጫን ማንበብ የሚችሉት በድረገጽ: https://www.vatican.va/roman_curia/congregations/cfaith/documents/rc_con_cfaith_doc_20201221_nota-vaccini-anticovid_en.html

የአውስትራሊያ ፋትዋ ምክር ቤት ኮቪድ/Australian Fatwa Council COVID-19 ክትባት ፋትዋ በቀን 13 የካቲት/February 2021 ዓ.ም ተሰጥቷል። ለፋትዋ/ Fatwa ክትባቱ የተሰጠው ከኮቪድ/ COVID-19 ክትባቶች ምርመራ ጥናትና ውይይት በኋላ እና ታማኝነትና ተቀባይነት ካላቸው የእስልምና እምነት ሀኪሞችና የህክምና ኤክስፐርቶች ውሳኔ በኋል ነው። የፋትዋ ምክር እንደ የእስልምና ህግ መሰረት የአውስትራሊያ ኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች የተፈቀደ እንደሆነ ነው። የአውስትራሊያ ፋትዋ ምክር ቤት ኮቪድ/Australian Fatwa Council COVID-19 ክትባት ፋትዋ/Fatwa የሚለውን ማንበብ ይችላሉ በድረገጽ: https://www.anic.org.au/fatwa-council/

በታላቁ ስይናጎጉ ስይድኒ Great Synagogue Sydneyበቀን 27 February 2021 ዓ.ም በወጣ ጽሁፋዊ መግለጫ የኮቪድ/COVID-19 ክትባቶችን ለመጠቀም እንደሚረዱ ነው። ጽሁፋዊ መግለጫውን ማንበብ የሚችሉት ድረገጽ: https://www.greatsynagogue.org.au/rabbiscorner.html

ስለ ኮቪድ/ COVID-19 ክትባቶች በቀን 13 ነሐሴ/August 2021 ዓ.ም የአውስትራሊያ ሞስሊም ህክምና ማህበር በጽሁፍ አሳውቋል። ለጽሁፋዊ መግለጫ በድረገጽ ላይ ማየት ይችላሉ: https://aimamed.com.au/feature-content/

## ስለ ኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች ጥያቄዎች ካለኝ ለማን ነው ማነጋገር የምችለው?

ስለ ኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች ከሆነ ሰው ጋር ለመነጋገር ከፈለጉ፤ ለአገር አቀፍ ኮሮናቫይረስ እርዳታ መስመር/Helpline በስልክ 1800 020 080 መደወል። ሆትላይን መስመር በእያንዳንዱ ቀን ለ 24 ሰዓታት ይቀርባል። ለአስተርጓሚ አገልግሎት በስልክ 131 450 መደወል።

በጤና ጥበቃ መምሪያ ድረገጽ ላይ በ63 ቋንቋዎች የቀረበ መረጃ የበለጠ መማር ይችላሉ፤ ድረገጽ www.health.gov.au/covid19-vaccines-languages።

እንዲሁም ለርስዎ ሀኪም ወይም ለአካባቢ ጤና ጥበቃ ባለሙያ ማነጋገር ይችላሉ።

ታማኝ እና ህጋዊ በሆኑ ምንጮች ማለት እንደ ጤና ጥበቃ መምሪያ ወይም ህክምና ጥራት አስተዳደር በኩል መረጃን እያገኙ መቆየት አስፈላጊ ነው።